# የህልውና ትግል ሌላው ገጽታ

የሰው ልጅ ለመኖር ሶስት መሰረታዊ ፍላጎቶች እንደሚያስፈልጉት እሙን ነው። እነዚህ መሰረታዊ ፍላጎቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከተፈጥሮ ሀብት ጋር በጥብቅ ይሚቆራኙ ናቸው። ከተፈጥሮ ሀብት ጋር። ለዚህም ነው የተፈጥሮ ሀብት ደህንነት ለሰው ልጅ ህልውና መቀጠል ትልቅ ዋስትና ነው። ተቃራኒው ከተከሰተ ደግሞ የሰው ልጅ ህልውና ክፉኛ አደጋ ላይ ይወድቃል።

ዛሬ ላይ በዓለም ደረጃም ሆነ በኢትዮጵያ እየተስዋለ ያለው የምርት መቀነስ፣የዝናብ እጥረት፣ ረሀብ፣ወዘተ በቢሊዮንና በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሰው ልጆች ህልውና አደጋ ላይ ሲወድቅ ይሰተዋላል። የተፈጥሮ ሀብት ልማትሥራ ለሰው ልጅ ህልውና መቀጠል ብቻ ሳይሆን ለግብርናው ዘርፍም የጀርባ አጥንት ነው። ሀገራት ወደ ተሻለ የኢኮኖሚ እድገት መሸጋገር የቻሉት የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራን አጠናክረው ማልማት በመቻላቸው ነው ። የተፈጥሮ ሀብትን በመጠበቅና በማልማት፣የአፈር ለምነትን በማሳደግ የምርትና ምርታማነት መጠን እንዲሻሻል በማድረግ የህዝብን የምግብ ዋስትናን ያረጋግጣል።

አማራ ክልል ከአገሪቱ የቆዳ ስፋት 15 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሚወስድ ሲሆን በበርካታ ተፈጥሮ ሃብቶች መታደሉ፣የተለያዩ የአየር ንብረት ቀጠናዎች ባለቤትነቱ፣በመሬት አቀማመጡ ለበርካታ ብዛ ህይወት መገኛ መሆኑን ብዙዎች የሚናገሩላት እውነት ነው። ። ይሁን እንጅ በአማራ ክልል የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራ በ1970ዎቹ መጀመሩን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በዚህ ዘመን የተጀመረ ቢሆንም የትኩረትና አተገባበር፣የተቀባይነትና ውጤታማነት እንከኖች ስለነበሩበት ለሶስት አስር አመታት ያህል ተቀዛቅዞ ቆይቷል። የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራው ከቆየበት ማንቀላፋት ወጥቶ በተሻለ አስተሳሰብ፣አደረጃጀትና አሰራር በትኩረት መልማት፣ መጠበቅና መጠቀም የጀመረው ከ2003 ዓ.ም ወዲህ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት የክልሉ የህልውና ጉዳይ መሆኑ ስለታመነበት በማሕበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ በየአመቱ እየተከናወነና ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበ ዛሬ ላይ ደርሷል። ለአብነትም በ2015 ዓ.ም 310 ሺህ ሄክታር መሬት የአፈርና ውኃ ጥበቃ ሥራ ለማከናወን ታቅዶ 357 ሺህ ሄክታር መሬት ተከናውኗል። በዚሁ በጀት አመት አርሶ አደሩ ከባለሙያው ጋር ባደረገው የጋራ ርብርብና የነቃ ተሳትፎ አራት ቢሊዮን ብር የሚገመት ጉልበቱን በነፃ ያበርክተ ቢሆንም ከ25 በመቶ በላይ የሚሆነው የተፈጥሮ ሀብት ልማት እና ጥበቃ ሥራ እደተጠበቀው አልተሰራም።በመልካም አንገት እንቅርት እዲሉ አበው የክልሉ አፈር ማዕድን እጽዋት ውአ ላይ ከፍተኛ አደጋ ከተደቀነበት አመታት

ተቆጥረዋል ፡፡ስለሆነም ይህ ጉዳይ ከወዲሁ መላ ካልተዘየደለት የሚደቀነው መጭ አደጋ የከፋ እደሚሆን ይገመታል፡፡

ከላይ በተገለጹት አመታት በክልሉ በተሰሩት የአፈርና ውኃ ጥበቃ እንዲሁም የተፋሰስ ልማት አፈጻጸሞች ደርቀው የነበሩ ምንጮች እንደገና ጎልብተዋል፤የአፈር ለምነት በመጠበቁና የውሃ እርጥበት መያዝ በመቻሉ የሰብል ምርታማነት ጨምሯል፡፡ የደን ሽፋን አድጓል፡፡ ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነፃ በተደረጉ ቦታዎች ላይም ወጣቶች ተደራጅተው ንብ በማነብ፣የወተት ላሞችን በማርባት፣ከብቶች በማደለብ እና የክሰል ምርት የሚሆኑ ዛፎችን በማልማት በኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል፡፡ ከእነዚህ ስኬቶች ጎን ለጎን የነበሩትን ክፍተቶችና ተግዳሮቶችን በማስተካከል ጥንካሬዎችን ደግሞ በማስቀጠል በየደረጃው ለዘርፉ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው፡፡ ያለፈውን በዚህ መልኩ መከታተልና ማስቀጠሉ እንደተጠበቀ ሆኖ የዘንድሮው የተፈጥሮ ሃብት ጥብቃና ልማት ስራ ጥር 15 ቀን 2017 ዓ.ም መጀመሩን የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ልማት ቢሮ አሳውቋል፡፡በልማት ስራው ከ4 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የሚሳተፍ ይሆናል፡፡ ከዘጠኝ ሺህ በላይ ተፋሰሶች ላይ ከ366 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ላይ የልማት ስራው እደሚከናወን ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች እየተሰሮ ነው ፡፡ ለዚህም ቀያሽ አርሶ አደሮችን የማሰልጠን፤ የስራ መሳሪያ የማዘጋጀትና ህብረተሰቡን የመነቃቃት/የመቀስቀስ ስራው ተጠናቆ ወደ ስራ ተገብቷ፡፡
በመጨረሻም የዚህ በጀት አመት ተፈጥሮ ሀብት ልማት ከሰው እና ከእንስሳ ስምሬት በመከለል በአጭር ጊዜ ውሰጥ እዲያገግም ከተደቀነበት መነቆ ተላቆ በታቀደለት ጊዜና ፍጥነት ልክ እንዲከናወን መላው የክልሉ አርሶ አደርና የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ እንዲሳካ እንረባረብ መልዕክታችን ነው፡፡

(ምንጭ፡-አብክመ ግብርና ቢሮ በራሪ ወረቀት፤አብክመ ግብርና ቢሮ ፋስቡክ ገጽ፤በኩር ድጎረ ገጽ ጋዜጣ፤አብክመ ኮሙዩኒኬሽን ፌስቡክ ገጽ፤ENA English፤Addis Standard ድህረ ገጽ ጋዜጣ)